


በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

# ነብያትን ተከተሉ

በሁለተኛው የአለም ጦርነት መጨረሻ ገደማ በዩናይትድ ስቴትስ የባህር ሀይል ውስጥ አገለገልኩ። በባህር ሀይል ውስጥ በዝቅተኛው ማእረግ፣ መርከበኛ ነበርኩ። ከዛም የመጀመሪያ ደረጃ መርከበኛ ለመሆን በቃሁ፣ ቀጥሎም ዮማን ሶስተኛ ደረጃ ለመሆን በቃሁ።

ሁለተኛው የአለም ጦርነት ተፈጸመ፣ እና ቀጥሎም እኔ ከስራ ወጣሁ። ነገር ግን ወደ ጦር ሀይሉ ብመለስ እንኳን፣ እንደ በስራ ላይ ያለ መኮንን ሆኜ ማገልገል እንደምፈልግ ወሰንኩ። “ማስወገድ የምችል ከሆነ፣ ከእንግዲህ ምስቅልቅል ያለ ኩሽና አይኖረኝም፣ ከእንግዲህ ወለሎችን መፈተግ የለም፣” ብዬ አሰብኩ።

ከስራ ከወጣሁ በኋላ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ባህር ሀይል መጠባበቂያን ተቀላቀልኩ። ሁሌ ሰኞ ምሽት ወደ ስልጠና ሄድኩ። በትምህርት ብቁ እንድሆን ጠንክሬ አጠናሁ። ሊታሰብ የሚችል ሁሉንም አይነት አእምሮአዊ፣ አካላዊ፣ እና ስሜታዊ ፈተና ወሰድኩ። በመጨረሻም፣ “በዩናይትድ ስቴትስ የባህር ሀይል መጠባበቂያ ውስጥ የአርማ ሀላፊነት እንድትወስድ ተመርጠሀል” የሚል የሚያምር ዜና መጣ።

ይህን በደስታ ለባለቤቴ፣ ፍራንሰስ፣ አሳየኋት እና “አደረኩት! አደረኩት!” አልኳት። እሷ አቅፋኝ፣ “እንዲሳካ በበቂ ሁኔታ ጠንክረህ ሰርተሀል” አለችኝ።

ከዛ ግን አንድ ነገር ተከሰተ። በአጥቢያዬ ኤጲስ ቆጶስ አመራር ውስጥ አማካሪ ሆኜ ተጠራሁ። የኤጲስ ቆጶስ የምክክር ስብሰባ ከባህር ሀይሉ የስልጠና ስብሰባ ጋር በተመሳሳይ ምሽት ነበር። መጥፎ አለመ ጣጣም እንደነበረ አወኩኝ። የባህር ሀይል እና የኤጲስ ቆጶስ ሀላፊነትን ለመቀጠል ጊዜ እንዳልነበረኝ አወኩኝ። ምን ማድረግ ነበረብኝ? ውሳኔ መሰጠት ነበረበት።

ጸለይኩበት። ከዛም ወጣት እያለሁ የካስማ ፕሬዘዳንቴ የነበረውን ሰው፣ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሀሮልድ ቢ. ሊ( 1899-1973)፣ በዛም ጊዜ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት አባል የነብሩትን ለማየት ሄድኩኝ። ከእሱ ጠረጴዛ ባሻገር ተቀመጥኩ። የባህር ሀይል ሀላፊነቱን ምን ያህል ዋጋ እንደምሰጠው ነገርኩት። በእርግጥ፣ የተቀበልኩትን የሹመት ደብዳቤ ግልባጭ አሳየሁት።

በነገሩ ላይ ጥቂት ካሰላሰለ በኋላ፣ እንዲህ አለኝ፣ “ወንድም ሞንሰን፣ እንደዚህ ነው ማድረግ ያለብህ። እንደ ኤጲስ ቆጶስ አመራር አባልነትህ ባለህ ጥሪ አማካኝነት በዩናይትድ ስቴትስ የባህር ሀይል መጠባበቂያ ውስጥ ሀላፊነትህን መቀበል እንደማትችል ለባህር ሀይል ጉዳዮች ቢሮ ደብዳቤ ጻፍ”

ልቤ ሰመጠ። ጨምሮም፣ “በሳን ፍራንሲስኮ ውስጥ ለአስራ ሁለተኛው የባህር ሀይል አውራጃ አዛዥ ጻፍ እና ከመጠባበቂያው መልቀቅ እንደምትፈልግ ንገራቸው።”

እንዲህ አልኩ፣ “ሽማግሌ ሊ፣ ስለ ጦር ሀይል አልገባህም። በእርግጥ እኔ አልቀበልም ካልኩ ሀላፊነቱን ለኔ መስጠቱን ይተዉታል፣ ነገር ግን አስራ ሁለተኛው የባህር ሀይል አውራጃ አይተዉኝም። በኮሪያ ጦርነት እየተቀሰቀሰ፣ ሀላፊነት የሌለው መኮንን በእርግጥም ይጠራል። በድጋሚ ከተጠራሁ፣ እንደ በስራ ላይ ያለ መኮንን ተመልሼ ብሄድ ይሻለኛል፣ ነገር ግን ይህንን ሀላፊነት ካልተቀበልኩ እንደዚያ አይሆንም። እንድቀበለው የምትፈልገው ምክር ይህ ስለመሆኑ እርግጠኛ ነህ.”

ሽማግሌ ሊ እጁን ትከሻዬ ላይ በማድረግ በአባታዊ መልኩ እንዲህ አለ፣ “ወንድም ሞንሰን፣ የበለጠ እምነት ይኑርህ። የጦር ሀይሉ ላንተ አይደለም።”

ወደ ቤት ሄድኩ። በእንባ የረጠበውን የሀላፊነት ጥሪ ከነ አጋዥ ደብዳቤው ወደ ፖስታው አስገባሁ እና መቀበሉን ተውኩት። ለአስራ ሁለተኛው የባህር ሀይል አውራጃ ደብዳቤ ጻፍኩ እና ከመጠባበቂያው የባህር ሀይል መልቀቂያ ጠየኩኝ።

የኔ ከባህር ሀይሉ መልቀቅ የኮሪያው ጦርነት ከመጀመሩ በፊት በተካሄደው በመጨረሻው ቡድን ውስጥ ነበር። የዋናው መስሪያ ቤት

የጦር ቡድን ለጦርነት እንዲዘጋጁ ተጠሩ። በኤጲስ ቆጶስ አመራር ውስጥ አማካሪ ሆኜ ከተጠራሁ ከስድስት ሳምንታት በኋላ፣ የአጥቢያዬ ኤጲስ ቆጶስ ሆኜ ተጠራሁ

የነብይን ምክር ሰምቼ ባይሆን ኖሮ፣ በውሳኔው ላይ ጸልዬ ባይሆን ኖሮ፣ በብዛት ለሰዎች ሞኝነት መስሎ የሚታየው የእግዚአብሔር ጥበብ ነው የሚለውን አስፈላጊው እውነታ ወደ ማመን ባልደርስ ኖሮ፣ ዛሬ የያዝኩትን የቤተክርስቲያን ሀላፊነት አልይዝም ነበር። [1] በሟችነት ኑሮ ውስጥ ልንማር የምንችለው አንድ ታላቅ ትምህርት ግን እግዚአብሔር ሲናገር እና ልጆቹ ሲታዘዙ፣ እነሱ ሁል ጊዜ ትክክለኛ ይሆናሉ።

ታሪክ በትንሽ ማጠፊያዎች ላይ ይዞራል ይባላል፣ እና ህይወታችንም እንደዚያው ነው። ውሳኔዎች እጣፈንታ ላይ ተጽእኖ አላቸው። ነገር ግን በውሳኔዎቻችን ውስጥ እርዳታ ቢስ ሆነን አልቀረንም።

የሰማይን ብርሀን ማየት ከፈለጋችሁ፣ የሁሉን ቻዩን እግዚአብሔር መነሳሳት እንዲሰማችሁ የምትፈልጉ ከሆነ፣ የሰማይ አባት እየመራችሁ እንደሆነ በውስጣችሁ እንዲሰማችሁ የምትፈልጉ ከሆነ፣ የእግዚአብ ሔርን ነብያት ተከተሉ። ነብያትን ስትከተሉ፣ ደህንነት ባለው ስፍራ ትሆናላችሁ።

ማስታወሻ
1. 1 ቆሮንጦስ 2፥14 ተመልከቱ።

---

### ከዚህ መልእክት ማስተማር

ልክ ፕሬዘዳንት ሞንሰን እንዳደረጉት፣ አብዛኛው ቤተክርስቲያን አባላት ከሐዋርያ ጋር አንድ ለአንድ ምክር አይቀበሉም። ነገር ግን አሁንም የነብያትን እና ሐዋርያትን ትምህርቶች ስንከተል ልንባረክ እንችላለን። ካለፈው አጠቃላይ ጉባኤ የፕሬዘዳንት ሞንሰንን መልእክት ማንበብን አስቡ (የመክፈቻ እና የመዝጊያ ንግግራቸውንም አስታውሱ)። ለድርጊት ቀጥተኛ ምሬትን ወይም ጥሪን ፈልጉ። የተማራችሁትን ከምትጎበኟቸው ጋር መወያየት ትችላላችሁ እና የፕሬዘዳንት ሞንሰንን ምክር የመተግበሪያ መንገዶችን አስቡ።

## ወጣቶች

# ለከባድ ምርጫዎች ምክር

ፕሬዘዳንት ሄነሪ ቢ. ኤይሪንግ፣ በመጀመሪያው አመራር የመጀመሪያ አማካሪ፣ የነብይ ምክርን ስለተከተለበት ጊዜ ተናገሩ። በአንድ አጠቃ ላይ ጉባኤ ወቅት፣ ፕሬዘዳንት ኤዝራ ቴፍት ቤንሰን (1899-1994) አባላት ከእዳ በተለይም ከብድር እንዲወጡ መከሩ።

ፕሬዘዳንት ኤይሪንግ አሉ፤ “ከስብሰባው በኋላ ወደ ባለቤቴ ዞር አልኩና ጠየቅኳት፣ ‘ያንን ልናደርግ የምንችልበት የሆነ መንገድ አለ ብለሽ ታስ ቢያለሽ.’ መጀመሪያ አልቻልንም ነበር።” ነገር ግን በአመሻሹ ለአመታት ለመሸጥ ሞክረው ያልተሳካላቸውን ንብረት አሰቡበት። “በእግዚአብሔር እና. . . በአገልጋዮቹ መልእክት ታመንን፣ ስለሆነም ስልክ ደወልን። . . . እስከዛሬ ድረስ በእግዚአብሔር እና በአገልጋዮቹ መታመኔን ያጠነከረ ምላሽ ነበር የሰማሁት።” በዛም ቀን ከእዳቸው ከፍ ያለ ዋጋ አንድ ሰው ለእነ ኤይሪንግ ንብረት ዋጋ አቀረበ። እነ ኤይሪንግ ወዲያው ከእዳ ነጻ ሆኑ (“Trust in God, Then Go and Do,” *Liahona*, Nov. 2010, 72–73 ተመልከቱ)።

መክፈል የሚያስፈልጋችሁ ቤት የተገዛበት እዳ ላይኖራችሁ ይችላል፣ ነገር ግን በስራ፣ ትምህርት፣ ሚስኦን፣ እና ቀጠሮ ዙሪያ አይነት አስቸጋሪ ውሳኔዎች የነብያት ምክር አሁንና ወዲያውም ሊመራችሁ ይችላል። ውሳኔ መስጠት ሲኖርባችሁ እንዴት ነቢይን መከተል እንደምትችሉ ከቤተሰባችሁ ወይም ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

በ© 2015 Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ)
*First Presidency Message, January 2015.* Amharic. 12581 506 ትርጉም

# የኢየሱስ ክርስቶስ ባህሪያት፥ ታዛዥ ልጅ

እምነት፣ ቤተሰብ፣ እርዳታ

*በጸሎት መንፈስ ይህንን መረጃ አንብቡት እና ምን እንደምታካፍሉ ለማወቅ ጣሩ። የአዳኝን ህይወት እና ተልእኮ መረዳት በእርሱ ያላችሁን እምነት የሚያሳድገው እና በሴቶች የቤት ለቤት ትምህርት ምክንያት የምትንከባከቧቸውን የሚባርከው እንዴት ነው? ለተጨማሪ መረጃ ወደwww.reliefsociety.lds.org ሂዱ።*

*ተከታታይ በሆነው የቤት ለቤት መልእክት ይሄ የአዳኝን ባህሪያት የያዘው ክፍል ነው።*

የኢየሱስስ ክርስቶስን የመታዘዝ ምሳሌ መከተል በእርሱ ላይ እምነታችንን ይጨምራል። የአስራሁለቱ ሐዋርያት አባል የሆኑት የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ጄፍሪ አር. ሆላንድ እንዲህ አሉ፣ "መጀመሪያ እና በአብዛኛው ክርስቶስ አባቱን መውደዱን እና መታዘዙን እናም ታማኝ ልጅ በሆኑ እሱነቱን አሳልፎ መስጠቱን ለመግለጽ መምረጡ ይገርም ይሆን. ታዛዥነት የሰማይ የመጀመሪያው ህግ ነው።"[1]

"እና ምንም አይነት በረከት ከእግዚአብ ሔር ስናገኝ፣ ቅድሚያ በተነገረው ህግ ላይ ታዛዥ በመሆን ነው"(ትናቃ 130፥21)። በመታዘዝ እና የአዳኝን የሀጢያት ክፍያ ሀይል ወደ ህይወታችን በመጋበዝ ወደ እግ ዚአብሔር ስንቀርብ መንፈሳዊ እድገታችን ይከናወናል።

"ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መርሆዎች እና ትእዛዛት ታዛዥ ሆነን ስንኳዝ፣" አሉ የአስራ ሁለቱ ሀዋርያት አባል ሽማግሌ ዲ. ቶድ ክሪስቶፈርሰን፣ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባለው ቃልኪዳን ውስጥ ቃል በገባው በረከቶች ያለማቋረጥ እንደሰታለን። እነዚያ በረከቶች በህይወት ጉዟችን በእኛ ላይ ከመደረግ ይልቅ እኛው ለማድረግ የሚያስፈልጉን መነሻዎች ያቀርቡልናል። ታዛዥነት በህይወታችን ላይ ታላቅ ቁጥጥር፣ ለመምጣት እና ለመሄድ፣ ለመስራት እና ለመፍጠር ታላቅ አቅም ይሰጠናል።"[2]

## *ተጨማሪ ቅዱሳት መጻህፍቶች*

ሉቃስ 22፥41-46፤ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 82፥10፤ 93፥28

## *ከቅዱሳት መጻህፍት*

"ቀጣይነት ባለው ለትእዛዛት በመታዘዝ የሚገኘው መንፈሳዊ ጥንካሬ ለሌላ ሰው ሊሰጥ ይችላል." ብለው የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት አባል ሽማግሌ ዴቪድ ኤ. ቤድናር ጥየቁ። "ግልጹ መልሱ. . . አይሆንም ነው"[3]

የአስርቱ ቆነጃጅት ታሪክ የዚህ መርህ ምሳሌ ነው። ሁሉም ቆነጃጅት "ሙሽራውን ለመቀበል" መብራታቸውን ሲወስዱ፣ አምስቱ ብቻ ልባሞች ነበሩ እና ` ዘይት ወሰዱ። ሌሎቹ አምስቶች ሰነፎች ነበሩ ምክ ንያቱም "ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙም።"

ከዛም እኩለ ሌሊት ላይ ውካታ ሆነ፥ "እነሆ ሙሽራው ይመጣል፤ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ።" ሁሉም ቆነጃጅት ማብራታቸውን ለኮሱ፣ ሰነፎቹ ግን ዘይት አልነበራቸውም። ለልባሞቹ ቆነጃጅት እንዲህ አሏቸው፣ "ፋኖሳችን ሊጠፋብን ነው፣ ከዘይታችሁ ስጡን"

ልባሞቹ ቆነጃጅት፣ "ምናልባት ለእኛ እና ለእናንተ ባይበቃስ፣ ይልቅስ ወደ ሚሸጡት ሂዱ እና ለእራሳችሁ ግዙ።" ሰነፎቹ ቆነጃጅት በሄዱ ጊዜ፣ ሙሽራው መጣ እና ልባሞቹ ቆነጃጅት አብረውት ገቡ እና "ደጁም ተዘጋ።"

(ማቴዎስ 25፥1–13).

ማስታወሻዎች

1. ጄፍሪ አር. ሆላንድ፣ "The Will of the Father in All Things" (Brigham Young University devotional, Jan. 17፣ 1989)፣ 4፣ speeches.byu.edu።
2. ዲ. ቶድ ክሪስቶፈርሰን፣ "The Power of Covenants፣" *Liahona*፣ May 2009፣ 21።
3. ዴቪድ ኤ.ቤድናር፣ "Converted unto the Lord፣" *Liahona*፣ Nov. 2012፣ 109።

### *ይህን አስቡበት*

ከቅዱሳን መጻሀፍት የታዛዥነት ጥቂት ምሳሌዎች የትኞቹ ናቸው.

በ© 2015 Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ)
*Visiting Teaching Message, January 2015*. Amharic. 12581 506 ትርጉም